ለክቡር አቶ ቀጀላ መርዳሳ

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

አዲስ አበባ

ለአቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ

የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ :- የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎትን የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ይመለከታል፤

የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 16 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 25 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከማክበር ሰላምታ ጋር!

በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ
ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

<u>በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር</u>

<u>የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት</u> አገልግሎት

<u>የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት</u>

የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት የተመደበለትን የመደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጁ፣ ደንቡ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት የተዘጋጁ የሂሳብ ሪፖርቶች፡-

- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣
- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣

- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት የ2015 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064 አንቀጽ 27 ሰራተኛን በተጠባባቂነት ማሰራትን በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ 1 ሁኔታዎች ሲያስገድዱ አንድን የመንግስት ሰራተኛ ለአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ ከፍ ያለ ደረጃ ባለው የስራ መደብ ላይ በተጠባባቂነት እንዲሰራ ማድረግ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በአብያተ መጻሕፍት መረጃ ሀብቶች አስተዳደር ላይ የሚሰሩት ሰራተኛ ከሐምሌ 1/2013 ጀምሮ በጡረታ የተሰናበቱ ሲሆን ቦታው ላይ የደረጃ እድገት እስኪወጣ ድረስ በተጠባባቂነት መድቦ ማሰራት በማስፈለጉ በደብዳቤ ቁጥር 11/5/ሠከ6/ በቀን 1/11/2013 ዓ.ም ጀምሮ ወ/ሮ ክብነሽ ገ/ስላሴ በሚያገኙት የወር ደመወዝ ላይ በልዩነት ብር 3,523.00 እየተከፈላቸው በአብያተ መጻሕፍት መረጃ ሀብቶች አስተዳደር በተጠባባቂነት ለአንድ አመት ተመድበው ያገለግሉ ሲሆን ሰራተኛዋ የአንድ አመት ጊዜ የሚያበቃው ሐምሌ 30/2014 ቢሆንም መመሪያ ከሚፈቅደው ጊዜ በላይ ከነሐሴ 1/2014 ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30/2015 ለስድስት ወራት በጠቅላላ ብር 17,615.00 የተጠባባቂነት አበል አላግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፣

2. የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ በወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥራዓት ግንቦት 1999 ዓ.ም በወጣው የሂሳብ መደብ የተሰጠ ትርጉም ይህ የወጪ መደብ በንግድ ሥራ ከተሠማሩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በመንግስት ባለቤትነት ስር ወይም ከመንግስት ውጭ ካሉ ተቋሞች ጋር የሚደረግን የሙያ አገልግሎት ውልን ያካትታል በማለት ይገልጻል፡፡ ስለሆነም መ/ቤቱ የመንግስትን መመሪያና ደንብ ተከትሎ ክፍያ የሚፈጽም መሆኑን ለማጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በተለያየ ጊዜ የሚዲያ

ባለሙያዎች በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ ላወያዩበት፣ ለመድረክ መሪ፣ ለአነቃቂ፣ ለመ/ቤቱ ሶፍትዌር ለጫኑበት እንዲሁም ፈተና ላወጡበት፤ ላረሙበት ወዘተ በሚል በድምሩ ብር 452,000.00 አላግባብ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን፡-

- ባለሙያዎቹ ስለመጋበዛቸው እና ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- አገልግሎቱን ለመስጠት የሚችሉ ስለመሆናቸው የትምህርት ዝግጅት ወይም የተለየ ተሰጥኦ ያላቸው ስለመሆኑ የሚያስረዳ ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ትክክለኛ የውል ሰጪና ተቀባይ መብትና ግዴታዎችን በሚገልጽና በምስክሮች በፊርማ የሚረጋገጥ ውል አለመኖሩ፤
- ለባለሙያዎች የሚከፈለው ክፍያ ወጥነት ያሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ የክፍያው መጠን በመመሪያ ያልጸደቀ መሆኑ፤

በመሆኑም ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እና 2 ከተገለጸው ምክንያት በስተቀር በእኛ አስተያየት የኢትዮጲያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ያሉት የሂሣብ ሪፖርቶች የተሰበሰበውን ገቢ የተፈጸመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ።

I. ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)

1. የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀትና የወጣው ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይተው በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሰያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ያዛል፡፡ ሆኖም ግን አገልግሎቱ በድምሩ ብር 3,739,710.85 የወጪ ምዝገባዎች በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

2. በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት መሥሪያ ቤቱ በ2015 በጀት ዓመት የተፈቀደው የወጪ በጀት አጠቃቀም ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለው በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ፡- በድምሩ ብር 36,550,017.73 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

II. ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች (Compliance Matters)፤

1. የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር3/2003 በአንቀጽ 22 የመንግስት ገቢ አሰባሰብ አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ 3 ላይ የመንግስት ገንዘብ ሊሰበሰብ የሚችለው ተከታታይ ቁጥር ባለውና ሚኒስተሩ ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ ወይም በሚንስትሩ ፈቃድ በሚዘጋጅው የገቢ ደረሰኝ ወይም ኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ መጠቀም እንደሚቻል፤እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 378/2008 ታሪፍ ባወጣው ደንብ መሰረት መሰብሰብ እንዳለበት በተደነገገው መሰረት ተግባራዊ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በተወሰደ የኦዲት ናሙና መ/ቤቱ የሚሰበስበውን ገቢ ገንዘብ ሚኒስቴር ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ መሰብሰብ ሲገባ በራሱ ስም ባሳተመው የገቢ ደረሰኝ ብር 432,973.23 የሰበሰበ መሆኑ፣

2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። መ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኢዲት ሲደረግ፡- በተለያዩ የሂሳብ መደቦች፡- በድምሩ ብር 122,314.72 በደንቡና በመመሪያው መሰረት ሳይወራረድ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ፣

II. **<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>**

1. በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት የበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ መከናወኑ እንዲሁም እስቶክ ካርድ(ቢን ካርድ) ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር የተመዛዘነ መሆኑን ለቋሚ እቃ ሙሉ በሙሉ መለያ ቁጥር የተሰጠ መሆኑን አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ መወገዳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

<u>በአላቂ እቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የሚገዛው ንብረት/እቃ ስቶር ስለመኖሩ በጹሁፍ የሚረጋገጥበት ወጥ የሆነ ስርዓት አለመኖሩ፤

- አዲስ 1 ኤር ኮምፕረሰር፣ መሰላል፣ የወንድ እና የሴት ቆዳ ጫማዎች፣ 3 የሴት እና 4 የወንድ ዣንጥላዎች፣ 5 አንሶላዎች፣ 72 ካልሲዎች፣ 6 አዲስ ኤልኢዲ መብራቶች፣ 2 የግርግዳ ቀለም፣ 2 የመኪና ፍሬቻ፣ የካሜራ ማጉያ(micro film scanner)፣ 1 ዲስክ ብሬክስ (disc Brakes)፣ 1 ቶነር መለያ ቁጥር 3320፣ 1 ቶነር ፎቶኮፒ መለያ ቁጥር 2525፣ ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ የደንብ ልብስ እና ጋውኖች፣ 19 ብትን ጣቃ ጨርቅ፣ ነጭ ጋውን 50 በጥንድ፣ 6 ቡኒ ጋውን፣ 3 ውስጥ ልብስ፣ 9 የወንድ ሙሉ ልብስ ያልተሰፋ፣ የውስጥ ልብስ ብትን ጨርቅ/ያልተሰፋ በሜትር የማይታወቅ፣ 23 የጋውን ብትን ጨርቅ፣ 1 የውሃ ባልዲ፣ የጽዳት ጓንት፣ ብዛት ያላቸው ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ የእጅ ጓንቶች፣ 14 የሴት ውስጥ ልብስ ብትን ጨርቅ፣ የተለያዩ ብትን ጨርቆች ቁርጥራጭ 3 ካርቶን እና 2 ማዳበሪያ፣ 9 የተሰፉ የወንድ ሙሉ ልብስ፣ 1 የዝናብ ካፖርት፣ 1 ሽሚዝ ሴፍቲ ጫማ እና ሴፍቲ ኮፍያ፣ 1 አዲስ ሳምሶናይት፣ መወገድ የነበረበት 1 ካርቶን የ2011 ቢን ካርድ፣ መወገድ የነበረበት 1 ካርቶን ሞዴል 22፣ 2 የካሜራ መብራት፣ የጎማ መንፊያ፣ 1 ካርቶን የተለያዩ መጽሃፍት፣ 1 የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1 ኮፒ ሆልደር፣ 13 የደረሰኝ ወረቀት፣ 1 ካሜራ፣ 3 የወንድ ካፖርት፣ 21 አዲስ የመጋረጃ ጨርቅ፣ የሚወገድ 2 ዩፒኤስ፣ 2 የሚወገድ የእርሳስ መቅረጫ፣የእጅ ባትሪ፣ የጠረጴዛ ካልኩሌተር፣ 2 አዲስ ትልቅ ፓንቸር እና 2 አዲስ ትንሽ ፓንቸር፣ 7 ላፕቶፖች ከእነ ቦርሳቸው ቋሚ ንብረት ጋር መገኘት ሲገባው አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የተገኘ ፣ 2 አጎበር፣ በሜትር የማይታወቅ ያልተሰፋ የውስጥ ልብስ፣ 10 ነጭ ፕላስተር ፣ 2 ማጭድ፣ 2 መቧጠጫ እና 2 መጋዝ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ በቆጠራ ሪፖርት ላይ ያልተካተቱ መሆኑ፤
- በተለያዩ ዓመት ተገዝተው ከሰራተኛው የተረፉ እና የ2015 በጀት አመት ዩኒፎርም ግዥ ተፈጽሞ ለሰራተኛ ሳይሰጥ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የተቀመጠ እንዲሁም ለሰራተኞች ተሸንሽኖ የሚሰጡ ዩኒፎርሞች በባለሙያ ተለክቶ የማይሰጥ በመሆኑ የተነሳ ሲሸነሸን ያለአግባብ ተቆራርጠው የተረፉ በመሆኑ ለብክነት ተዳርገው የተቀመጡ መሆኑ፤

በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት፤

- በግምጃ ቤቱ ያሉ ተመላሽ ንብረቶች ተመላሽ ሲደረጉ ንብረቶቹ ያሉበት ሁኔታ ማለትም የሚሰራ፣ የማይሰራ እና ቢጠገን ሊሰራ የሚችል በሚል ተለይተው ያልተቀመጡ መሆኑ፤
- መወገድ ያለባቸው ንብረቶች በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤ አዲስ 12 ቫክዩም ክሊነር በጽዳት ሰራተኞች ተጠይቆ የተገዛ ቢሆንም ስራ ላይ ሳይውል ከአንድ አመት በላይ የተቀመጠ፣ 26 ሞኒተሮች፣ ብዛት ያላቸው ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ የተለያዩ የቢሮ ጠረጴዛዎች (የኮምፒዩተር ጠረጴዛዎች)፣ ብዛት ያላቸው የኮምፒዩተር ስፒከሮች፣ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ የካሜራ ስታንዶች፣ ብዛት ያላቸው የመኪና ባትሪዎች፣ ብዛት ያላቸው የሚሰራና የማይሰራ የቆሻሻ ቅርጫቶች፣ ከክፍሎች ጥያቄ መሰረት የተገዙ የተለያዩ የፕሪንተርና የፎቶኮፒ ቀለሞች እንደታሸጉ ኦዲተሩ መቁጠር በተቻለው መጠን የተቆጠሩ በቁጥር 86 ቢሆንም ብዛት ያላቸው ቶነሮች ሌሎች ንብረቶች ተጭነውባችው መቁጠር ያልተቻሉና ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳትሰጥ የቆመ ሞተር ሳይክል የሰሌዳ ቁጥር 0012፣ የሚሰራ የውሃ በርሜል፣ ብዛት ያላቸው ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ ፕሪንተሮች፣ 71 የግርግዳ ቀለሞች፣ 2 የውሃ ማጣሪያ፣ ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ ዩፒኤስ፣ ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ የመኪና ጎማዎች፣ ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ ላሜራዎች፣ ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ ፒቢሲዎች፣ ቁጥራቸው በወል የማይታወቅ የወረቀት መጠረዣዎች፣ ብዛት ያላቸው ቬንትሌተሮች፣ ብዛት ያላቸው ስታብላይዘሮች፣ ብዛት ያላቸው የማይታወቁ የተለያዩ ዲቫይደሮች፤
- ሰራተኞች እጅ ላይ ያለ ንብረት ቆጠራ ቢደረግም በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ተቆጥረው ያልተመዛዘኑ መሆኑ፣

ሌሎች፤

- አላቂ እና ቋሚ ንብረቶች በአንድ ባለሙያ ብቻ(ወ/ሮ አጸደ ተፈራ) የሚያዝ መሆኑ እንዲሁም ገቢ እና ወጪም በአንድ ሰራተኛ የሚሰራ መሆኑ፤
- የካፌ ንብረት ሆኖ የመ/ቤቱ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የተገኙ 30 ወንበሮች፤
- የእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ መገኘት ሲገባው በግቢው ውስጥ ያለአግባብ የተቀመጡ ላሜራዎች፣የብረት ጋሪዎች፤

- የመጽሃፍት ቆጠራ የተካሄደ አለመሆኑ እና ዘግቶ ቆጠራ ለማካሄድ ከ2 ወር በላይ ስለሚፈጅ ተገልጋይን ላለማጉላላት እና መጽሃፍቶቹ ከዚህ ውጪ መገኘት ስለማይቻል ቆጠራ ማካሄድ ያልተቻለ መሆኑን ገልጸዋል ሆኖም የጥንታዊ ቅርስ ክምችት ክፍል ግን ቆጠራ የተካሄደ መሆኑን የገለጹልን ቢሆንም የቆጠራ ሪፖርት ያልተያያዘ /ያልተገኘ/ መሆኑ፤
- በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከመስሪያ ቤቱ መኪኖች ውጭ የተለያዩ ብዛት ያላቸው መኪኖች በቤተ መጽሐፍት ተጠቃሚዎችን ምክንያት በማድረግ በግቢ ውስጥ የሚቆሙ ሲሆን አብዛኛው መኪኖች በቤተ መጽሐፍት የማይጠቀሙ እና ሌሎች የንግድ መኪኖች ያለ አገልግሎት የሚቆሙ መሆኑና ምንም አይነት ፍተሻ የማይደረግ መሆኑ፣

2. በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሁለት መሰረት ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት እና ሉሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ስለመሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለመመዝገብ፣ ለማከናወን፣ ለማጠቃለል እና ሪፖርት ለማድረግ እንዲያስችላቸው በኮምፒዩተር በታገዘ የመረጃ ሥርዓት ላይ ተስማሚ ቁጥጥሮችን መዘርጋት እና መጠበቅ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መ/ቤቱ የሚጠቀምበት የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ (ICT) የመረጃ ሚስጥር ጠባቂነት ታማኝነትና አቅርቦት ሊያረጋግጥ የሚችል የመረጃ ቴክኖሎጂ ቀርጾ ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-
   - የመ/ቤቱ መረጃ/ሠነድ ከሥጋት ነፃ የሚሆንበት የፀደቀ (IT Security policy) የሌለው መሆኑ፤
   - በመ/ቤቱ ውስጥ የተዘጋጀና የጸደቀ “User Account Management Standard” የሌለ መሆኑ፤
   - መ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አደጋ ሲያጋጥም መልሶ የሚቋቋምበት እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ
   - በመ/ቤቱ አደጋ ቢደርስ ተብሎ የተዘጋጀ ወይንም ፎርማል የሆነና ተዘጋጅቶ የተቀመጠ መመሪያ የሌለ መሆኑ፤
3. በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ

ለመለየት የውስጥና የውጪ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም አገልግሎቱ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ፣

4. ክትትል ኦዲት፡

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች፤

- ከቀን 3/13/2013 ጀምሮ ለተከታታይ 15 ቀናት ለመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች በድምሩ 1,208,765 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በቂ ማስረጃ አለመቅረቡ፤ የሰአት መቆጣጠሪያው ሰልጣኙ በትክክል በስልጠናው ስለመገኘቱ በሚመለከተው ክፍል ያልተረጋገጠ መሆኑ፤ስልጠናው ሳይጠናቀቅ ክፍያው በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑ፤
- የንብረት ስራ ክፍልና የተሽከርካሪ ስምሪት የውስጥ አሰራር መመሪያ ላይ ውይይት የማድረግና የማነቃቂያ ስልጠና ከሚያዚያ 4 ቀን 2014 ጀምሮ ለ14 ቀናት በአዳማ ከተማ ለማከናወን በደረሰኝ ቁጥር 0005719 በቀን 7/8/2014 ብር 571,326.00 ክፍያ ሲፈጸም፤የስልጠናው የክፍያ ሰነድ ያልተዘጋጀና የሰአት መቆጣጠሪያው በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ መሆኑ፤ ለስልጠና የሚያስፈልገውን የመስተንግዶና የአዳራሽ ኪራይ ክፍያ ሰነድ የሌለ መሆኑ ፤ ስልጠናው ሳይጠናቀቅ ክፍያው በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑ፣
- በደረሰኝ ቁጥር0006157 በቀን ሰኔ 20/10/2014 በባህርዳር ከተማ የንባብ ሳምንት ቡክ ፌር እና ኤግዚቢሽን ተሳታፊዎች ብር 199,710.00 ለተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ በተመለከተ፤ የውሎ አበል መክፈያ ሰነድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤ ከውጪ የተጋበዙ ተሳታፊዎች የጥሪ ደብዳቤ ያልቀረበ በመሆኑ የሚከፈላቸውን የውሎአበል ለመተመን የሚያስቸግር መሆኑ፤ በወጪ ማዘዣው ላይ የውሎ አበል የመነሻ ቀን እንጂ የመመለሻውን ቀን ያልተገለጸ በመሆኑ፤ ጉዞው ምን ያህል ቀን እንደፈጸሙና የምን ያህል ቀን ታስቦ እንደተከፈለ ባልታወቀበት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፡፡
- በደረሰኝ ቁጥር0005270 በቀን የካቲት21/2014 ብር 117,396.00 እና የወጪ ደረሰኝ ቁጥር0006206 ሰኔ 23/2014 ብር 48,576.00 ለተፈጸመው ክፍያ፤ በተመለከተ፤ የክፍያ ሰነዱ በሚመለከተው ሃላፊ ያልጸደቀ ከመሆኑ በተጨማሪም

የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ሰነድ በመመሪያው መሰረት ያልተዘጋጀ ሆኖ መገኘቱ የውሎ አበል መጠየቂያ ሰነድ ላይ ለስራ የተሰማሩበት ቀን ከመቼ እስከ መቼ እንደሆነ የተገለጸ ባለመሆኑ የማወራረጃ ሰነዱ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያለመቻሉ፣የክፍያ ሰነዱ ያረጋገጠው እና ያጸደቀው በአንድ ሰው መሆኑ ፣

በጠቅላላ ድምር ብር 2,383,693.00 ለተፈጸመ ክፍያ በቂ የሆነ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

የ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች፡-

- ብር 3,119.14 መ/ቤቱን ለለቀቀ ሰራተኛ የተከፈለ፤
- ብር 91,714.75 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ ውሎ አበል፤
- ብር 2,109,004.51 የግንባታ ሂሳብ በተመለከተ፤

ተገልጸ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት 2016 ዓ.ም